# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን፣

www.ginbot7.org

ቁጥር 19 መስከረም 15 2001 ዓ.ም


## ህዝባዊ ንቀቱ እና አገራዊ ክህደቱ የመጨረሻው ጫፍ ላይ ደርሷል

**"በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲ ዎች መኖራቸው አያስፈልግም"** መለስ ዜናዊ

ከዕለት ዕለት በሀገር እና በህዝብ ላይ እየፈፀመ ባለው ግፍ ያለ አንዳች ህዝባዊ መሰረት እርቃኑን የቀረው የመለስ አገዛዝ፣ለነፃው ፕሬስ እና ለሲቪክ ማህበራት ሲጎነጉን የሰነበተውን ሸምቀቆ ካጠናቀቀ በሁዋላ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወደማጥፋት እርምጃ ተሸጋገረ። ኢ.ህአዴግ፣ ከስልጣን ዋዜማ ጀምሮ ስለ ዲሞክራሲ እና ስለ መድብለ ፓርቲ ስርዓት አስፈላጊነት እና ወሳኝነት ሲደሰኩር የከረመ ፓርቲ ቢሆንም፣የድርጅቱ ሊቀመንበርመለስ እና አፈ ቀላጤያቸው በረከት ሰሞኑን ለአባሎቻቸው '' በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖራቸው አያስፈልግም ''የሚል ገለፃ ሲያደርጉ ሰንብተዋል።ያለ አንዳች ሀፍረት ፣ከውስጣዊ ማንነታቸው ወደመነጨው ወደዚህ እርምጃ የተንደረደሩት፣አገሪቱን እና ህዝቦቿን አፍነው በያዙበት ሁኔታም ቢሆን፣ በቀጣዩ ምርጫ መሸነፋቸው አይቀሬ መሆኑን በማረጋገጣቸው እንደሆነ ታውቋል።
ሰሞኑን በአዋሳ እየተካሔደ በነበረው የኢ.ህአዴግ 7ኛ ድርጅታቂ ጉባኤ ላይ መለስ-'' በ ኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖራቸው አያስፈልግም፣ የአርሶ አደር አገር እንደመሆኗ፣ የአርሶአደሩ የዕድገት ጥያቄ በኢ.ህአዴግ ብቻ የሚመለስ ነው" ብለዋል።
ይህን ማለታቸውን ተከትሎ ከአንዲት ተሳታፊ -" ይህ አቋም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለአገሪቱ ዲሞክራሲ የሚያደርጉትን ጥረት አያሰናክልም ወይ? " በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄም፣ -" የብዙ ፓርቲዎች መኖር ዲሞክራሲ መኖሩን የሚያመለክት ይሁን አይሁን እስካሁን የታወቀ ነገር የለም" በማለት ሌሎች ፓርቲዎችን ለማጥፋት ያላቸውን አቋም ይፋ አድርገዋል።
ስልጣናቸው አደጋ ውስጥ የገባ ባልመሰላቸው ጊዜ-"የተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር ለምንገነባው ዲሞክራሲ እና ለዕድገታችን ወሳኝ ነው'' እያሉ ዓለማቀፉ ህብረተሰብን ና የኢትዮጵያ ህዝብን ሲያታልሉ ፣ የኢ.ህአዴግ አባላትን ደግሞ ሲያስጨበጭቡ የኖሩት መለስ፣ ዛሬ በማናቸውም ምርጫ ቢሆን ስልጣናቸው አደጋ ውስጥ መውደቁ አይቀሬ መሆኑን ሲረዱ፣ "ዕድገት የሚመጣው በአንድ ፓርቲ ስለሆነ መድብለ ፓርቲ አይሰራም" በማለት ዓለምን እና የኢትዮጵያን ህዝብ ሲያስቆጡ፣እነዚያኑ በትዕዛዝ ያሰሯቸው የሚመስሉትን አባሎቻቸውን ዛሬም በግልባጩ ንግግራቸው አስጨብጭበዋቸዋል።አስተያየታቸውን የሰጡ የፖለቲካ ተኝታኞች_"ይህ በ ኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በዓለማቀፉ ህብረተሰብም ጭምር፣ከንቀት በመነጨ የተፈፀመ አስነዋሪ ክህደት መሆኑን በመጥቀስ፣ወደለየለት አምባገነንነት እየገሰገሰ ያለውን የመለስ አገዛዝ ማስተንፈስ የሚቻለው በተባበረ የህዝብ ክንድ እና ተመጣጣኝ በሆነ የትግል ስልት መሆኑን አስምረውበታል።

---

**ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ**

**በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም**

**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2:00 እስከ 2:30 ፣ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

---

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በኢትዮ ኤርትራ ድንበር አንዣቦ የሰነበተው የጦርነት ስጋት ጨምሯል

### የመለስ አገዛዝ ዳግም ጦርነት እንደሚከፍት ምልክቶች እያሳየ ነው

የመለስ አገዛዝ ከኤርትራ ጋር ዳግም ወደከፉ ደም አፋሳሽ ጦርነት ለመግባትና አያሌ ወገኖቻችንን ደመ ከልብ ለማድረግ ሰሞኑን በከፍተኛ ሁኔታ እየተዘጋጀ መሆኑን ጉዳዩን በቅርበት የከታተሉ ምንጮቻችን ጠቆሙ።"የኤርትራ መንግስት የሶማሊያ ዳግም ነጻነት ተዋጊዎችን በዋነኝነት እየረዳ እና ያስታጥቃል" በማለት በተደጋጋሚ ክስ ሲያሰማ የሰነበተው የመለስ አገዛዝ፣ በምስራቁ ግንባር በተደጋጋሚ እየደረሰበት ባለው አሳፋሪ እና ዘርፈ ብዙ ኪሳራ ሽንፈቱ አይቀሬ መሆኑን ካረጋገጠ ወዲህ ፣በኤርትራ ላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀቱን ምንጮቻችን አክለው ገልፀዋል።
መለስ ሰሞኑን በቃለ ምልልስ መልክ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሰጠው ድርጅታዊ መግለጫ፣"አንሚ ከ አካባቢው ከለቀቀ በሁዋላ ጦርነት ይቀሰቀሳል የሚል ግምት በብዙዎች ዘንድ ቢኖርም፣ ጦርነት ሊጀመር አልቻለም።ጦርነቱ ያልተጀመረበትን ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?" በማለት ለተዘጋጀለት ለራሱ ጥያቄ መልስ በሰጠበት ጋዜጣዊ መግለጫ-"የኤርትራ መንግስት አቅም ስለሌለው፣እኛ ደግሞ ስለማንፈልግ ነው" ሰሞኑን በአዋሳ በተካሄደው የኢ.ህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ደግሞ-"የጎረቤት አገር መሪዎች ሳይቀሩ ባገኙን ጊዜ ከኤርትራ መንግስት ጋር በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እስከመቼ ትኖራላችሁ? ፅናቱን ይስጣችሁ"እስከማለት ደርሰዋል ማለቱን አመልክተዋል።
መለስ አክሎም-" በእርግጥም ከመንደር ጎረምሳ ጋር ዝንተ ዓለም እየተነታረክን መኖር አንችልም" ማለቱን የገለፁልን የጉባዔው ተሳታፊዎች ምንጮቻችን፣ በጉባኤው የኢትዮ ኤርትራን ሁኔታ አስመልክቶ መለስ ያደረው አጠቃላይ ገለፃ ፣በሁለቱ አገሮች መካከል በቅርቡ ጦርነት አይቀሬ መሆኑን የሚያመላክት ነው ብለዋል።
ዘግይቶ በደረሰን መረጃ መሰረት የመለስ አገዛዝ አስመራን በሁለት ሰዓት ውስጥ መቆጣጠር የሚያስችል ስትራቴጂ አለኝ ማለቱ ተሰምቷል።ይህ የመለስ ንግግር በአስመራ ነዋሪዎች ዘንድ መድረሱም ታውቋል።ሆኖም"በሁለቱ አገሮች መሀከል ጦርነት ከተጀመረ አካባቢው አደጋ ውስጥ ይገባል" ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፣እንደ አንዳንድ ታዛቢዎች ገለጻ ግን፣ "የመለስ ንግግር ከተለመደው ባዶ ጩኸት የተለየ አይደለም።በሱማሊያ በኩል የደረሰበትን ሽንፈት በኤርትራ መንግስት ላይ ይበልጥ በበቀል ስሜት እንዲነሳ ቢገፋፋውም፣ኤርትራን ለመግጠም ኢኮኖሚያዊም ሆነ የህዝብ ድጋፍ እናም የሰራዊቱ ሞራላዊ አቅም እንደሌለ ራሱ መለስ በደንብ ስለሚረዳው አይሞክረውም" ይላሉ።ከስምንት ዓመታት በፊት በሁለቱ አገሮች መካከል በተደረገው ከባድ ጦርነት፣ ከሁለቱም ወገን ከ70 እስከ 100 ሽህ በላይ ወጣቶች መሞታቸው ይታወቃል።

# ርእሰ አንቀጽ

## ከወጋገኑ በፊት ያለው ጨለማ ጥቅጥቅ ፤ ከማእበሉ በፊት ያለው ፀጥታ ጥልቅ ፤

ከውልደት በፊት ያለውም ምጥ አስጨናቂ ነው ይላል የሃገራችን ሰው ። ዛሬ ኢትዮጵያችን ከጎሁ በፊት ካለው ጨለማ ፤ ከግልግሉ በፊት ካለው ምጥ ፤ ከማዕበሉ በፊት ካለው ርጭታ ጋር ትመሳሰላለች ። ይህን ሃቅ ያልተረዱ ቢኖሩ የወያኔ የጨለማ ሃይሎች ብቻ ናቸው ። የማይነጋ መሰሎአቸዋል ። ሃዋሳ ላይ "እልፍ ሆነናል ዛሬስ እልፍ ሆነናል" ሲዘምሩ ከርመው ፤ የኢትዮጵያን የነፃነት ብርሃን እንዴት እንደሚያዳፍኑ ተስማምተው ጉባኤያቸውን አጠናቀዋል ። እያንዳንዱን ዕቁብና ዕድር እንዴት ሰርገው እንደሚገቡ ፤ እያንዳንዱን ነፃ አሳቢ ዜጋ እንዴት እንደሚያንበረክኩ ፤ ከነጋዴነት እስከ ዱክትርና እንዴት በነርሱ እርጥባንና መቁነን ብቻ እየተለካ መሰጠት እንዳለበት ተስማምተው ፈፅመዋል ። አዎን ፈፅመዋል ። የዘረኛ አገዛዝ ፍፃሜ መንግስት መቃረቡ ግን አልገባቸውም ።

"ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነውን" በዘመሩበት የጥንት የታጋይ አፋቸው ፤ ዛሬ "እልፍ ሆነናል ዛሬስ እልፍ ሆነናል"ን ሲዘምሩ ከየት ጀምረው የት እየጨረሱ መሆናቸው የገባቸው አይመስሉም ። ድርጅታቸውን ወደ አንድ ታላቅ የስለላ መዋቅር ለመቀየር መስማማታቸውን አልተረዱትም ። መላውን ህብረተሰብ ሰቅዞ የሚይዝ ፤ በቁም የሚበላ ተባይ ለመሆን መወሰናቸው አልገባቸውም ። ከዛሬ 25 አመታት በፊት መንግስቱ ሃይለማርያም ከ500 ብር በላይ ደሞዝ የሚከፈለውን ሁሉ ሰማያዊ መርዶፋ አስለብሶ ፤ በኢሰፓ አባልነት ዜጎችን ሁሉ ለማሰመዝገብ ባስገደደበት ሰአት ፤ የፍፃሜውን ቁልቁለት መንደርደር የጀመረበትም ቅፅበት ነበር ። ህብረተሰቡን በሙሉ የኢሰፓ አባል ለማድረግ ሲወስን ፤ ፓርቲውና መንግስቱን ለጠላቶቹ ጭምር ማጋለጥ ስለተገደደ ፤ ምስጢር ባከነ ፤ መተማመን ጠፋ ፤ ውድቀቱ ተፋጠነ ። ዛሬ መለስም የተያያዘው "አዲስ ፈሊጥ" ያው መንግስቱ ያቆለቆለበትን የአምባገነኖች ገሃነም ነው ። አስገድዶ በመለመለ ቁጥር ይበልጥ እየመነመነ ለመሄዱ ዋስትናው ነው ።

መለስ በዘንድሮው ጉባኤው "ሰባት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በደደቢት በረሃ የጀመሩት የትጥቅ ትግል እነሆ በአራት ሚሊዮን አባላት የታቀፈ ፓርቲ ለመሆን በቅቶአል" እያለ ኣዋጅ አስነግሮአል ። ያልገባው ነገር ግን "ለካስ ይሄም አለ?" የሚሉ ወጣቶች በተራቸው በሃገራቸው ታሪክ አይተውት የማያውቁትን ዘረኛ አገዛዝ ፡ ከጅማም ፤ ከሃዋሳም ፤ ከጎንደርም ፤ ከሃረርም ፤ ካዲሳባም ዩኒቨርሲቲዎች ልክ እንደርሱ ሰባት ሰባት ሆነው እየተማከሩ በትውልድ ሃገራቸው ወንዞችና ተራሮች ፤ በጊቤ ፤ በአዋሽ ፤ በተከዜ ፤ በከሰም ፤ በአመያ ፤ በሆሮ ጉድሩ ፤ በደብረ ብርሃን ወንዞችና ተራሮች "ነፃነት ወይም ሞት" የፈከሩ ቀን ፤ ደግሞም እየቆረጡ ነው ፡ ትግሉ 17 አመት ሳይሆን ፤ 17 ወራት እንደማይፈጅ አልተረዳውም ። ስላልተረዳውም በተያያዘው የእብሪት መንገዱ እየከነፈ ይገኛል ። በዚያው ልክ ውድቀቱም እየተፋጠነ ። ልቦና ቢኖራቸው የመለስ ጋሻ ጃግሬዎች ከሱማሌ ሽንፈታቸው በተማሩ ነበር ። ለነፃነቱ የሚሰንፍ ህዝብ በታሪክ ታይቶ እንደማያውቅና ፤ ኢትዮጵያውያንም የመጀመሪያዎቹ እንደማንሆን ለምን አልገባቸው አለ? ፈጣሪ ሆይ አስተዋይ ልቦና ስጣቸው !!

**አገራዊና ዓለማቀፋዊ ክህደት** ፣ከገጽ 4 የዞረ

ልብ በሉ፤ መለስ እና በረከት ይህን ሲሉ የተማመኑት አንድ ነገር ብቻ ነው-ፈጣሪን ሳይሆን ከፈጣሪ በላይ የሚያመልኩትን ጠመንጃ። ስለዚህ ጠመንጃ ህዝብን ሊያሸንፍ እንደማይችል ተግባራዊ ትምህርት የመስጠቱ ድርሻ እና ሀላፊነት የኢትዮጵያ ህዝብ ይሆናል። እንደ ግንቦት 7 ፅኑ እምነት፤ ይህ ለከት ያጣ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ክህደት እንደ አመጣጡ ከወዲሁ በተባበረ ክንድ ሊደቆስ ይገባል። ስለዚህ፤ በጥይትና በረሀብ የሚፈጀን አንሶት ወደለየለት የጨለማ ጉድጓድ እየከተተን ያለውን የመለስን አገዛዝ ለማስወገድ፤ ኢትዮጵያውያን ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን ለትግል እንነሳ። ትግላችን በሞራል፣ በህግና በህሊና ተቀባይነት ያለው ብቻ ሳይሆን፤ አገራዊና ህዝባዊ ክህደትን ለመቅጣት ፤ በአንፃሩ ፍትህን፣ ነፃነትን እና ዲሞክራሲን ለማረጋገጥ የሚደረግ ስለሆነ በልበ ሙሉነትና በኩራት ልንነሳ ይገባል።በዚህ አጋጣሚ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ዕውን መሆን የምትሹ ወዳጅ አገራት፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ተቋማት፤ የመለስ አገዛዝ፤ ፍፁም ክህደት የፈፀመው በዲሞክራሲ ላይ መሆኑን በመገንዘብ፤ እንዲሁም ዲሞክራሲን የረገጠ መንግስት የፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ አጋር ሊሆን እንደማይችል በማስታወስ እና የመለስ አገዛዝ የአፍሪካ ቀንድን ሰላም ከማረጋገጥ ይልቅ የራሱን ግዛትም ሆነ ቀጣናውን ያለፋታ እያሸበረ ያለ ሀይል መሆኑን በመረዳት፤ ይህን ዕብሪተኛ እና አምባገነን ሀይል ለማስወገድ በዲሞክራት ሀይላት የሚደረገውን ትግል ከወዲሁ ትደግፉ ዘንድ ግንቦት ሰባት ለፍትህ፣ ለነፃነት እና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ጥሪውን ያቀርባል።

**ዲሞክራሲ ያሸንፋል!**

## የነገር ጥግ

ባለፈው መስከረም 7 ቀን ሰባተኛውን የኢህአዴግ ጉባኤ ለመካፈል የተመረጡት የኢህአዴግ አባላት አዋሳ የሚገኘው መሰብሰቢያ አዳራሽ ሲደርሱ፤ ከኮንፈረንስ አዳራሹ ማዶ “ ጃ ያስተሰርያል” የሚለው የቴዎድሮስ ካሳሁን ወይም የቴዲ አፍሮ ዜማ በከፍተኛ ድምፅ ያስተጋባ ነበር።በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነውና ስለ ብሔራዊ መግባባት የሚያጠነጥነው ይህ ሙዚቃ፤ ዓፄ ሀይለሥላሴን ከማንሳት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተፈራረቁት የኢትዮጵያ አብዮቶች፤ የመሪዎችን መቀያየር እንጅ ህዝብ የናፈቀውን ለውጥ ሊያ መጡ እንዳልቻሉ በአሳዛኝ ቅላፄ ያስተጋባል።

**“ በ 17 መርፌ የጠቀመው ቁምጣ፣**
**ለለውጥ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ሲወጣ፣**
**እንደ አምናው ባለ ቀን ያምናውም ተቀጣ፣**
**አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ? “** በማለት።
(ምንጭ ፎርቹን ጋዝጣ)



**የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፡-** POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## የሚገነፍል፡ድስት፡የሚያበላሸዉ፡እራሱን፡ነዉ

በአፍሬም፡ማዴቦ

ታዋቂዉን፡ድምፃዊ፡ቴዎድሮስ፡ካሳሁንን፡አስሮ፡በአገሪቱ፡ብቸኛ፡
ዘፋኝ፡እንደመሆን፡የዳዳዉ፡ወያኔ፡ንግዱም፡ዘፈኑም፡አልበቃ፡ብ
ሎት፡ሰሞኑን፡ለብቻ፡የሚያስደንስ፡እብደት፡ጀምሮታል።አብዮታ
ዊ፡ዲሞክራሲን፡እንደ፡መጽሐፍ፡ቅዱስ፡
ቃል፡ካልተቀበላችሁ፡እያለ፡በነጋ፡በጠባ፡ሕዝብን፡መነትረክ፡የያዘ
ዉ፡ወያኔ፡ዛሬ፡እብደቱ፡ጠንቶበት፡ከመለስ፡ሌላ፡
መሪ፡ከኢህአዴግ፡ሌላ፡ፓርቲ፡የለም፡ማለት፡ጀምሮአል፡፡እኔን፡የ
ሚያስፈራኝ፡ይህ፡አይደለም፡እብድ፡ፈርቼም፡አላዉቅ፡እጠነቀቃለ
ሁ፡እንጂ፡፡
እኔንም፡ሆነ፡የአገሬን፡ሕዝብ፡የሚያሳስብን፡ነገር፡ቢኖር፡ምኒልክ፡
ቤተመንግስት፡የገባ፡ሁሉ፡
የሚነግስ፡እየመሰላቸዉ፡አቶ፡መለስ፡እንደ፡አህመድ፡ቦካሳ፡ቀዳማ
ዊ፡መለስ፣አባባ፡ስብሃት፡ደግሞ፡በስተእረጅናቸዉ፡አልጋወራሽ፡እ
ገሌ፡ተብለዉ፡እንዳያርፉት፡ነዉ፡፡ዲሞክራሲን፡አንግቦ፡ለህዝብ፡የ
በላይነት፡ቆሜያለሁ፡የሚል፡መንግስት፡
ወደደም፡ጠላ፡ምርጫ፡የሚባለዉን፡የህዝብ፡ዉሳኔ፡የመቀበል፡ግዴ
ታ፡አለበት፡፡ዲሞከራስያዊ፡ምርጫን፡ለማካሄድ፡
ደግሞ፡ከፋም፡ለማ፣የተቃዋሚ፡ፓርቲዎች፡መኖር፡የማይዘለል፡ሀ
ቅ፡ነዉ።ከምክንያት፡አልባ፡ኩርፊያ፣ጥላቻና፣ግልምጫ፡ዉጪ፡ሌላ
፡ምንም፡አይነት፡ገንቢ፡ግኑኝነት፡ከተቃዋሚዎች፡ጋር፡መፍጠር፡
የማይሻዉ፡ወያኔ፡ተቃዋሚ፡ፓርቲዎችን፡
የሚጠላዉ፡የስልጣን፡ፍቅር፡ስለተጠናወተዉ፡ሲሆን፣ትክክለኛ፡ም
ርጫን፡የሚፈራዉ፡ደግሞ፡እዉነትን፡ሰለሚፈራ፡ነዉ።
ለወየኔ፡እንደምርጫ፡በተለይ፡እንደግንቦቱ፡ምርጫ፡እዉነትን፡ፍር
ጥርጥ፡አድርጎ፡የነገረዉ፡አካል፡የለም።የከርሞ፡ሰዉ፡
ይበለን፡እንጂ፡
እኔ፡ብቻ፡ባዩ፡ወያኔ፡አገራችን፡ኢትዮጵያን፡በቅርብ፡ጊዜ፡ከምርጫ
-የለሽ፡ዲሞከራሲ (*no-election democracy*)
ወደ፡ፓርቲ-የለሽ፡ዲሞክራሲ (*no-party democracy*)
ለማሸጋገር፡ቆርጦ፡የተነሳ፡ይመስላል።

ሰሞኑን፡ያለ፡የሌለ፡ሀይሉን፡አሰባስቦ፡ከመገናኛ፡ብዙሀን፡ጋር፡ዉጊ
ያ፡የገጠመዉ፡ወያኔ፡ከፐሬስና፡ከነፃ፡ጋዜጦች፡ጋር፡የጀመረዉን፡ግ
ብግብ፡የህዝብን፡ልሳን፡የሚዘጋ፡አዋጅ፡በማወጅ፡በአሸናፊነት፡የተ
ወጣ፡ቢመስለዉም፣ዛሬ፡በአገር፡ዉስጥና፡ከአገር፡ዉጭ፡የሚኖሩ፡ለ
ግል፡ሳይሆን፡ለአገር፡ጥቅም፡የቆሙ፡የቁርጥ፡ቀን፡ኢትዮጵያዉያ
ን፡በሚያደርጉት፡ትብብር፡የነፀዉ፡ፕሬስ፡ትግል፡ወደ፡ከፍተኛ፡ም
ዕራፍ፡በመሸጋገር፡ላይ፡ነዉ።ወያኔ፡ወደደም፡ጠላ፣አገራችን፡ኢት
ዮጵያ፡
የምታካሄደዉ፡የዲሞክራሲ፡ግንባታ፡ጥረት፡ሰምሮና፡በህዝብና፡በ
መንግስት፡መካከል፡የሚጣጣም፡ግኑኝነት፡ተፈጥሮ፡
አገራችን፡ፈጣን፡እድገት፡ማስመዝገብ፡የምትችለዉ፡በነፃነት፡እን
ደፈለገ፡መንቀሳቀስ፡የሚችል፡የፕሬስ፡አካል፡ሲኖር፡
ብቻ፡ነዉ።ነፃና፡የበለፀገ፡ህብረተሰብን፡ለመገንባት፡በሚደረግ፡ጥረ
ት፡ዉስጥ፡የፕሬስ፡ነፃነት፡በራሱ፡ግብ፡ሳይሆን፡ወደ፡
ዋናዉ፡ግብ፡የሚያደርስ፡ፍቱን፡መሳሪየ፡ነዉ።ይህንን፡መሳሪያ፡ከ
ተጠቀሚዉ፡ህብረተሰብ፡መቀማት፡እድገትን፡ከመዋጋት፡ተነጥሎ
፡አይታይም።ግሚሱ፡ጋዜጠኛ፡እስር፡ቤት፡ግሚሱ፡ተሰድዶና፡የተቀ
ረዉ፡ደግሞ፡አንገቱን፡ደፍቶ፡በፍርሀት፡በሚኖርበት፡
አገር፡የፕሬስ፡ነፃነት፡ቀርቶ፡ፕሬስ፡ራሱም፡አለ፡ለማለት፡አያስደፍ
ርም።

ዲሞክራሲን፡በተግባር፡መመሪያቸዉ፡ያደረጉ፡አገሮች፡ሁሉ፡ሁለ
ት፡ግዙፍ፡ሀይል፡አላቸዉ፤እነሱም፡ፕሬስና፡ህዝብ፡
ናቸዉ።ከህዝብ፡ዉስጥ፡ተፈትኖ፡ያልወጣና፡ፕሬስ፡ህዝባዊ፡ህልዉ
ናዉን፡ያላረጋገጠለት፡ማንኛዉም፡ሀይል፡ጊዜያዊና፡
ተሸናፊ፡ነዉ።ለዚህ፡ነዉ፡ገና፡ከጅምሩ፡መሸነፉን፡በሚገባ፡የተገነዘ
በዉ፡ወያኔ፡አግአዚያዊ፡በትሩን፡በህዝብና፡በፕሬስ፡
ላይ፡በተከታታይ፡የሚያሳርፈዉ።ዛሬ፡የኢትዮጵያ፡ጋዜጦች፡የሚሰ
ማቸዉን፡መጻፍ፡ኢትዮጵያዉያን፡ደግሞ፡
የሚፈልጉትን፡ማንበብ፡አይችሉም።በአገራችን፡በኢትዮጵያ፡የሚ
ታየዉ፡ቴሌቭዥን፣የሚነበበዉ፡ጋዜጣና፡የሚደመጠዉ፡ሬዲዮ፡ሁሉ
ም፡ለህዝብ፡ይዘዉ፡የሚቀርቡት፡የወያኔን፡ርካሽ፡ፕሮፓጋንዳ፡ብቻ፡
ነዉ።የወያኔን፡የዜና፡ማሰራጭያ፡
አዉታሮች፡የማይከታተል፡ኢትዮጵያዊ፡ምንም፡የሚቀርበት፡አይ
መሰለኝም፣የሚከታተል፡ቢኖር፡ደግሞ፡የተሳሳተ፡መረጃ፡ነዉ፡የሚያ
ገኘዉ።እዚህ፡ላይ፡አንድ፡የማንወደዉና፡የማንፈልገዉ፡እዉነት፡ቢ
ኖር፡የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ጋዜጣ፡ቢያነብ፡ ባያነብ፣
ሬድዮ፡ቢያዳምጥ፣ባያዳምጥ፣ቴሌቭዥን፡ቢያይ፡ባያይ፡ስለአገሩ፡ም
ንም፡መረጃ፡ማግኘት፡አለመቻሉ፡ነዉ።

ሌላዉ፡ወያኔን፡ካጋለጡትና፡እርቃኑን፡ካስቀሩት፡ጠባያቹ፡አንዱና፡
ዋነኛዉ፡እንደ፡አየር፡በየደቂቃዉ፡የሚተነፍሰዉ፡
ዉሸቱ፡ነዉ።የዛሬዉስ፡ዉሸት፡ቆሞ፡ይሄዳል፡ትለን፡ነበር፡እናቴ፡የ
ማይመስል፡ነገር፡በሰማች፡ቁጥር።የዛሬዉን፡
የወያኔን፡ተራ፡ዉሸት፡በሰማች፡ቁጥር፡ምን፡እንደምትል፡ባላዉቅም
፤ሩጫ፡አገር፡ሲያኮራ፡እንጂ፡ሲያበላሽ፡
ሰላላየች፡ይሮጣል፡እንደማትለን፡ግን፤ይገባኛል።እስኪ፤ልብ፡በሉ፡
ቅንጅት፡ደርግ፡ነዉ፣ኦነግ፡አሸባሪ፡ነዉ፣ኢትዮጵያ፡
ዉስጥ፡ረሀብ፡የለም፣ምርጫዉ፡የኢትዮጵያን፡ህዝብ፡ፍላጎት፡ያገናዘ
በ፡ነዉ፡እያለ፡እርቃኑን፡የቀረ፡ከሀዲነቱን፡
እየነገረን፡የሚደብቀን፡ወያኔ፡ስለ፡እራሱ፡የሚያወራዉ፡አንዲት፡ቅን
ጣት፡እዉነት፡ሳይኖረዉ፡እንዴት፡አድርጎ፡ነዉ፡
ስለ፡ሌሎች፡እዉነት፡የሚነግረን?

የኢትዮጵ፡ህዝብኮ፡ከወያኔዎች፡ጋር፡አብሮ፡መጉዋዝ፡የማይፈልገዉ
፡ህዝብ፡
ትናንትናና፡ከትናንት፡ወዲያ፡ሰምቶት፡የተቀበለዉን፡እዉነት፡ወያ
ኔዎች፡ከነገ፡ወዲያ፡ሰምተዉት፡ስለሚያጣምሙት፡ ነዉ።
እብሪት፡የወጣጠረዉ፡ወያኔ፡ጆሮዉን፡በእብሪቱ፡ሸፍኖት፡ነዉ፡እንጂ
፡በአገራችን፡በኢትዮጵያ፡ጉዳይ፡
ተቃዋሚዎችና፡ወያኔ፡የየራሳቸዉ፡አስተያየት፡እነጂ፡የየራሳቸዉ፡ሀ
ቅ፡ሊኖራችዉ፡አይችልም።
አርቆ፡አስተዋይነታችንና፡ልበ፡ሰፊነታችን፡አደብ፡አስገዝቶን፡እስከ
ዛሬ፡ታግሰናል።ከአሁን፡በዉዋላ፡
ግን፡የነፃነት፡ፍላጎታችንና፡የፍትሀ፡ጥማታችን፡ሳይረካ፡የሚያቆመ
ን፡ምንም፡ሀይል′እንደሌለ፡
ስለምናምን፡የነፃነት፡ጉዞ፡ጀምረናል።ይህንን፡ጉዞ፡መቀላቀል፡የእያ
ንዳንዱ፡ነፃነት፡ፈላጊ፡ኢትዮጵያዊ፡የግልና፡የጋራ፡
ሀላፊነት፡ነዉ።ወድ፡ወገኖቹ፡የአገራችን፡ህዝብ፡መብቱንና፡ነፃነቱን
፡በቀማኞች፡ተቀምቶአል። ይህንን፡ህዝባችን፡
በሀይል፡የተቀማዉን፡ነፃነትና፡መብት፡ቀማኞቹ፡ከተዋጠላቸዉ፡በ
ሠላማዊ፡ድርድር፡አሻፈረን፡ካሉ፡ደግሞ፡በትግል፡ማስመለስ፡ኢትዮ
ጵያዊ፡ግዴታችን፡ነዉ።ነፃነቱንና፡መብቱን፡ተቀምቶ፡ተደላድሎ፡የ
ሚኖር፡ህዝብ፡ዕጣ፡መደቡ፡ዝንተ፡
ዓለም፡ባሪያ፡ሆኖ፡መኖር፡ብቻ፡ነዉ።ከዚህ፡አይነቱ፡ዉርደትና፡የቁ
ም፡ሞት፡ልዑል፡እግዚአብሄር፡ያድነን!
የአዛኝ፡ቅቤ፡አንጉዋቹ፡ወያኔ፡የእዉነት፡እርቃንዋን፡መቅረት፡ያሳዘ
ነዉ፡ይመስል፡ስራዉ፡ሁሉ፡በነጋ፡በጠባ፡እዉነትን፡
መሸፋፈን፡ሆኖአል።የወያኔ፡ዉሸት፣ትዕቢት፣ጭካኔና፣ተንኮል፡አድጎ
፡አድጎ፡መሸከም፡የማይገባን፡ደረጃ፡ላይ፡ደረሶአል።
ወተት፡የተጣደበት፡ድስት፡ከምድጃዉ፡ላይ፡ሲወርድ፡መቀዝቀዙ፡ላ
ይቀር፡ይገነፍላል፤የሚገነፍል፡ድስት፡ደግሞ፡
የሚያበላሸዉ፡እራሱን፡ነዉ።

# የፖለቲካ ትንትና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## አገራዊና ዓለማቀፋዊ ክህደት ሊቀጣ ይገባል

ጋቼዬ

የመለስ ቡድን በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለሀያላን አገሮች ቃል በመግባቱ ፤ከስልጣን ዋዜማ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተለይ በአሜሪካ መንግስት ከፍተኛ ድጋፍ ሲደረግለት ቆይቷል።ሆኖም፤ በታሪክ እንደታዩት ሌሎች አምባገነኖች ሁሉ፤ ቃሉ- ከባዶ ዲስኩርነት አላለፈም ።በተለይ ራሱ ዋነኛው አሸባሪ ሆኖ በዓለማቀፉ ፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ ሽፋን ስር ከጳጳሱ ቄሱ ሆኖ ምዕራባውያንን ሲያታልል የከረመው የመለስ አገዛዝ፤በተደጋጋሚ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሚፈፅምበት ጊዜ ፤ከሀያላን አገሮች የሚደርስበት ተፅዕኖ፤ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር ይህን ያህል የጎላ ስላልሆነ፤ያለምንም ልጓም በወንጀል ላይ ወንጀል እየጨመረና የአምባገነንነት ጡንቻውን እያፈረጠመ መጥቷል።

ሌላው ቀርቶ፤ በግንቦት 97 ምርጫ የደረሰበትን ሽንፈት በሀይል በመቀልበስ ፤ሰልፍ የወጡ አያሌ ዜጎችን በከባድ መሳሪያ ሲያስጨፈጭፍ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ የሲቪክ እና የሙያ ማህበራት መሪዎችን በጅምላ ሲያስር፤ ቆንጠጥ የሚያደርግ እርምጃ ለመውሰድ የደፈረ አካልም ሆነ አገር ባለመኖሩ ፤ እነሆ ዛሬ ነፃ ፕሬስንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨርሶ ለማጥፋት አፋኝ እና ጨቋኝ ህጎችን ከማውጣት ተላልፍ፤ በአደባባይ **"መድብለ-ፓርቲ ብሎ ነገር የለም"** እስከማለት ደረሰ። መለስ፤የቀራቸው ነገር ቢኖር በነካካ አፋቸው ልክ እንደ ኮሎኔል መንግስቱ **"የአሜሪካው ኢምፔሪያሊዝም ይወድማል!"** ማለት ብቻ ነው።ለነገሩ " **መድብለ ፓርቲ በ ኢትዮጵያ አይሰራም ፤ የአርሶ አደሩ ጥያቄ በ አንድ ፓርቲ የሚመለስ ነው** " ብሎ ተቃዋሚ ፓርቶዎችን ለማጥፋት መነሳት፤ ከኮሎኔል መንግስቱ በከፋ መልኩ የኢትዮጵያን ህዝብ፤ ዋሽንግተንን እና ምዕራባውያንን መስደብ፣ መናቅ፣መካድ እና ማበሻቀጥ ነው።

የዛሬን አያርገውና ቀደም ሲል የመለስ እና የኢህአዴግ ወዳጅ የነበሩት አሜሪካዊው ባለስልጣን ኸርማን ኮህን፤ የግንቦት 97ቱ ምርጫ በሀይል በተቀለበሰ ማግስት፤ ከፍ ባለ ቁጣ እና ሀዘን የመለስ አገዛዝ የፈፀመው ድርጊት የዋሽንግተንን አስተዳደር እንደመካድ የሚቆጠር መሆኑን አስምረውበታል።እንደ ኸርማን ኮህን የወቅቱ ገለፃ፤ መለስ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለመገንባት ቃል በመግባታቸው፤ ከስልጣን ዋዜማ ጀምሮ የአሜሪካ መንግስት በተደጋጋሚ በገንዘብና በልዩ ልዩ መንገድ ድጋፍ አድርጎላቸዋል።ከኮሎኔል መንግስቱ ስንብት ዋዜማ ጀምሮ ዋሽንግተን ለአዲሱ የአዲስ አበባው አስተዳድር ድጋፍ ያደረገችው፤ በኢትዮጵያ እውነተኛ ዲሞክራሲ ሰፍኖ የማየት ፍላጎት ስላላት ነው ያሉት ኮህን፤ ሆኖም ፤ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ ምሰሶ የሆኑት ነፃ ምርጫ፣ ነፃ ፕሬስ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባልጠበቅነውና ባልገመትነው ሁኔታ ለከፍተኛ ጥቃት ተዳርገዋል ብለዋል። ይህም መንግስታቸውን እና ዲሞክራሲን እንደመካድ የሚቆጠር መሆኑን አስረድተዋል።

የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ መስራች እና አመራር የሆኑት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ከወራት በፊት ብራሰልስ ላይ ለአውሮፓ ህብረት የፓርላማ አባላት ባሰሙት ንግግር፤" **መለስ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዓለማችን ቁጥር አንድ አምባገነን መሪ ይሆናል"** ማለታቸው ይታወሳል።በግንቦት 97 በተካሄደው ምርጫ ለመምረጥ የተመዘገበው ህዝብ 26 ሚሊዮን ሲሆን፤ከነዚህ መካከል 11 ሚሊየኑ ዋነኛውን ተፎካካሪ ፓርቲ ቅንጅትን የመረጡ ናቸው።የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ እና ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎችም የተጭበረበረውን ሳይጨምር ከ 60 በላይ የፓርላማ ወንበር ማግኘታቸው ሲታይ፤ ከ 26 ሚሊየኑ መራጭ ህዝብ፤ የገዥው ፓርቲ ድርሻ ጭብጥ እንደማይሞላ ለመገንዘብ ፎርሙላ የሚያስፈልገው ሂሳብ አይጠይቅም። በወቅቱ ዶክተር ብርሀኑ እንዳሉት ሰልፉን አሳምሮ ወደ ጥሩ ተቃዋሚ ፓርቲነት ጎራውን መለየት የነበረበት ኢህአዴግ፤ ፍፁም ሊታመን በማይችል፣ ክህደት በተሞላበት እና ከድንጋጤና ከጭካኔ የመነጨ ሀይል በተቀላቀለበት ሁኔታ በደም ተነክሮና በደም ተጨማልቆ ወደዛው በደም ወደተበከለው የስልጣን ወንበሩ አመራ።

አገዛዙ፤ ከተፈጥሮአዊው የበቀል ባህሪው በመነሳትም፤ በሰላማዊ ፍልሚያው እንዳያንሰራራ አድርጎ በዘረረው የኢትዮጵያን ህዝብ ላይ ሳያሰልስ መጠነ- ሰፊ ጥፋት ሲፈፅም ሰነበተ። የተቃዋሚ ፓርቲ ቢሮዎችን ሲያሽግ፣ ንብረታቸውን ሲዘርፍ፣ አባሎቻቸውን ሲገድል እና ሲያስር ከረመ። በሚችለውና ባለው አቅም ሁሉ የዲሞክራሲ ምሶሶዎችን ሲገዘግዝ፣ የነፃነት ማገሮችን ሲነቃቅል እና የፍትህ ካስማዎችን ሲነቃቅል ቆዬ።የራሱን ጡንቻ ያለልክ አግዝፎ ሁሉንም ቁሉቁል መመልከት ቀጠለ። ፍርድ ቤቱም፣ ዐቃቤ ህጉም፣ ከሳሹም ዳኛውም፣ ፈራጁም፣ ይቅር ባዩም፣ ምርጫ ቦርዱም፣ ፈቃድ ሰጪውም ፣ፈቃድ ከልካዩም፣ ባለሀብቱም፣ ነጋዴውም ......ሁሉም እሱ ሆነ።"ምሉዕ በኩልሄ እኔ ነኝ" አለ።

ይህ አዝማሚያ እንደ አመጣጡ ልጓም ካልተበጀለት ማቆሚያ ሊኖረው እንደማይችል ካለፉት ተግባራዊ ተሞክሮዎች በመነሳት የማያወላዳ ግንዛቤ ላይ የደረሱ ዜጎች ፤እንደ ግንቦት ሰባት ዓይነት ንቅናቄ በመመስረት አገዛዙን በሁለገብ የትግል ስልት ሊፋለሙት ሲነሱ፤ ሌሎች ደግሞ ለሰላማዊ ትግል ያለው መንገድ ምንም እየጠበበ እና አላላውስ እያለ ቢመጣም ፤ ባለፈው የትግላቸው መንገድ ለመታገል ወስነው ቀጣዩን ምርጫ በትዕግስት እየተጠባበቁ ይገኛሉ።ግንቦት 7 የሁሉንም ሀሳብ እና መንገድ ያከብራል፤ ከዚያም ባሻገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ በአገራችን ዲሞክራሲን ዕውን ለማድረግ ያላቸው ትልም፤ በስኬት እንዲደመደምላቸው ጥልቅ ምኞቱ ነው።ሆኖም፤ አገዛዙ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ላይታረቅ ተጣልቷልና ወይም የኢትዮጵያ ህዝብ ሰማይ ቢከነበል የመለስን አገዛዝ ሊመርጥ ቀርቶ በይሁንታ ሊቀበለው እንደማይችል ተገንዝቦታልና፤ እንዲህም በታፈነበት ሁኔታ ተቃዋሚዎች በቀጣዩ ምርጫ እንዲሳተፉ አልተፈለገም። አገዛዙ ወትሮም ተሸናፊ ስለሆነ ፤በዚሁ ሁኔታም ቢሆን ዳግም እንደሚሸነፍ አውቆታላ።ለዚህ ነው የምርጫው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ነፃውን ፕሬስ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የማጥፋቱ ዘመቻ በስፋት የቀጠለው።

መጀመሪያ በፕሬሶች ቀጥሎ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሸምቀቆውን ያጠበቀው፤ ሆኖም ከስልጣን ስስቱ እና ከፍርሀቱ ማየል የተነሳ በወሰደው ዓለምን ያሳዘነ እርምጃ ፋታ ሊያገኝ ያልቻለው የመለስ አገዛዝ፤ እነሆ ለዘመናት ስለ ዲሞክራሲ እና የዲሞክራሲ መገለጫ ስለሆነው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ሲለፍፍ የኖረውን ቲዎሪ፤ ያለምንም ሀፍረትና መሸማቀቅ በአንድ ጀምበር በማጠፍ **"መድብለ ፓርቲ ብሎ ነገር የለም"** የሚል ያፈጀ ነጠላ ዜማ ለቋል። **"ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው አንድ ፓርቲ፤ እርሱም ኢህአዴግ ብቻ ነው"** ብለውናል- መለስና አፈቀላጤው በረከት በግላጭ።በአደባባይ። በሰገነት። **"ቢያንስ በቀጣዩ 50 ዓመታት ኢህአዴግ ኢትዮጵያን መምራት አለበት"** ብለዋል- በኢት ጵያ ህዝብ ልብ ውስጥ ሙት የሆነው ኢህአዴግ። ወንጀለኛው፣ ሰው በላው፣ ሙሰኛው፣ መለስ ራሳቸው ከአመታት በፊት እንዳሉት የበሰበሰውና የበከተው ኢህአዴግ። ህዝባዊ መሰረት ናፍቆት በአየር ላይ እየራደና እየተንቀጠቀጠ ያለው ኢህአዴግ።

፤ወደገጽ 2 ዞሯል